ግንቦት 21 ቀን 2016 ዓ/ም

የቅዱስ ሲኖዶስ አጀንዳን በተመለከተ የሚያወያዩ አወዛጋቢ ነጥቦችን በማንሳት ንቃታችን ለማሻሻል የቀረበ አስተያየት

ሰባት አበው ሊቃነ ጳጳሳትን የመወያያ አጀንዳውን እንዲያረቅቁ ተሰይመዋል። በምን መሥፈርት ተሰየሙ? ለቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ታማኝ እንደሆኑ ከዚህ ቀደም ባሳዩት አቋም ተገምግመዋል? የሚለተሉት ሀሜቶችና ምልከቶች ያሉባቸው ሰዎች እንዴት አጀንዳ መራጭ ሆኑ?

አጀንዳ ቀራጮች	**ለኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ያላቸው ታማኝነት**
1.ብፁዕ አቡነ ማርቆስ	? ቅባትን በጎጃም እንዲለማ የእረኝነት ኃላፊነታቸውን ያልተወጡና ---- የሚታሙ
2.ብፁዕ አቡነ ቀሌምንጦስ	? ሰሜን ሸዋ የሚካሄደውን እልቂት በዝምታ የሚከታተሉና ማዘናጊያ ዜና እያስነገሩ የሚኖሩ፤ ከተሐድሶና የፖለቲካ ሥርዓት ጋር ግኙኝነት እንዳላቸው የሚታሙ
3.ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ	? እረኝነታቸው፥ ---- ሌሎች ነገሮችም ላይ ጥያቄ የሚነሳባቸው
4.ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ	? ለጸረ ቤተ ክርስቲያን አብይ አህጠድ ታማኝነት በማሳየት የፓትሪያርኩን መግለጫ በመግለጫ ውድቅ በማድረግ ያሳዩ
5.ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ	? አፍቃሪ ተሐድሶ ተደርገው የሚታሙ
6.ብፁዕ አቡነ ሩፋኤል	7ኛ ፓትርያርክ ኦሮሞ ይሁን፥ ንጹሕ ኦሮሞ ጳጳስ ሾምንላችሁ በሚሉ ኢክርስቲያናዊ ንግግሮችና ፖለቲካዊ አገልጋይንት የሚታወቁ
7.ብፁዕ አቡነ ገብርኤል	የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና በመጣስ የብሔር ቤተ ክህነትና ብሎም ሲኖዶስ እንዲመሠረት የሚሠራውን ከሐዲ “አቃቤ ሃይማኖት” ብለው በቤተ ክርስቲያን በመቀለድ አቋማቸውን የገለጡ በአብይ አህምድ ፊት የፖለቲካ ታማኝነታቸውን ያሳዩ

አጀንዳዎቹስ ከምንገኝበት ሁለገብ መከራ አንጻር አግባብነት አለው?

አጀንዳ	**ወቅቱን ያገናዘበ አግባብነት**		የአግባብነት መኖርና አለመኖር ከወቅቱ አንጻር ሲገመገም (መግለጫ)
	አለው	**የለዉም**	
1. የቅዱስ ሲኖዶስ ዓመታዊ የሥራ ክንውንን በተመለከተ	☑		መደበኛና የተለመደ አሠራር ሲሆን ያለፈውን ዓመት ቃለ ጉባኤ አፈጻጸም፥ ያጋጠሙ ችግሮችና የቤተክርስቲያን ምላሽ፥ ለቀጣዩ እቅድና አፈጻጸም ምን ትምህርት መወሰድ አንደሚገባው የሚብራራበት አጀንዳ በመሆኑ አግባብነት አለው
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማትን አስመልክቶ ከቤትና ሕንጻ አስተዳደርና ልማት ድርጅት የቀረበ ሪፖርት በተመለከተ		☒	ይህ አጀንዳ በመነኮሳእ ጉባኤ የሚፈታ ሳይሆን በሕግ አዋቂዎች፥ በኦርቶዶክሳውያን የፖለቲካ ንቅናቄዎችና ማኅበራት በመሆኑ፡- የሕግ ባሙያዎችን መመሪያ መስጠጥ፥ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር መንግሥት በሕግና አዋጅ ስም የሚያካሄደውን ጥቃት ማስቆም በሚቻልበት አጀንዳ መተካት።
3. የሃይማኖት ረቂቅ አዋጅ በተመለከተ		☒	
4. የገቢዎች ባለሥልጣን የወሰነውን የግብር አከፋፈል ሁኔታ በተመለከተ		☒	
5. አገር አቀፍ የምክክር ኮሚሽንን በተመለከተ		☒	አገር አጥፊ፥ ጸረ ኦርቶዶክስ፥ ዘረኛና ከፋፋይ መንግሥት ዕድሜውን ለማራዘም በመሠረተው መፍትሔ የማይሰጥ “ምክክር” የሚባል ጨዋታ አንስቶ ከመነጋገር ትክክለኛው አጀንዳ መሆን የነበረበት”- “ኦርቶዶክስን ዒላማ ያደረገ የፖለቲካ ሥርዓትን ኦርቶዶክሳውያን እንዴት አንድ ሆነው እንሚቋቋሙትና ሲኖዶሱ እንዴት እንደሚመራው”
6. ወደ ውጭ ሀገር ለአገልግሎት የሚላኩ አገልጋዮችን በተመለከተ		☒	
7. የ2017ዓ.ም በጀት ማጽደቅን በተመለከተ	☑		**ዘመኑን በሚዋጁ አገልግሎቶች ላይ ያተኮሩ እቅዶችና ቅድሚያ** የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመለየት በጀት መደልደል በባለሙያ ተከናውኖ --- ጉባኤው ይሁንታ ይሰጣል
8. የስዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅን በተመለከተ		☒	በመደበኛ መዋቅር ውክልና የሚያልቅ በመሆኑ አጀንዳው አያስፈልግም

9. የምግባረ ሠናይ ጠቅላላ ሆስፒታል ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተ		☒	
10. የኢ/አ/ተ/ቤ/ክርስቲያን አንድነት ገዳም ጎብረት መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተ		☒	በቋሚ ሲኖዶስ፥ በሊቃውንት ታይቶ የሚአልቅና ለማጽደቅ ብቻ የሚቀርብ መሆን ነበረበት
11. የጋሞጎፋ ሀገረ ስብከት ተብሎ የሚጠራበት ስም ቀርቶ የጋሞና አካባቢው ዞኖች ሀገረስብከት አርባ ምንጭ ተብሎ ይጠራልኝ በማለት የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ		☒	በዚህ መከራ ግዜ ይህ አጀንዳ ቦታ መያዝ ያልነበረበት ከንቱ ነገር ነው
12. የጋሞና አካባቢው ዞኖች ሀገረ ስብከት ስለ ዚጊቲ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ		☒	
13. አሲኤን ቴሌቭዥን አስመልክቶ የቀረበ ጥናት በተመለከተ		☒	ከዚህ ቀደም በተወሰነው መሠረት ብቻ የሚፈጸም አንጂ አጀንዳ መሆን አይገባዉም
14. የብፁዓን አባቶች ዝውውር ጥያቄ በተመለከተ		☒	በዚህ መከራ ግዜ አጀንዳ መሆን አልነበረበትም። ብፁዐን አባቶች ከተሾሙበት ሀገረ ስብከት ውጭ ዝውውር አርቶዶክሳዊ ትውፊት አይደለም፥ (ሚስት ፈትቶ ሌላ እንደማግባት ያለ ነውር ነው) ቀኖናው ይስተካከል በሚል መተካት የሚገባው አጀንዳ ነው
15. የእነ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ (ዶ/ር) ማመልከቻን በተመለከት		☒	በሕግ የሚፈጸም እንጂ የሲኖዶስ አጀንዳ አይሆንም። በተጨማሪ መእመናን በንቅናቄ የሚፈቱት ይሆናልና አጀንዳው ተመሳሳይ ጉዳዮችን አንድ ላይ ጠቅልሎ በሕግና በአሠራር ደረጃ ውሳኔ ላይ የሚአደርስ ሆኖ መቀረጽ ይኖርበታል
16. ከመሪ እቅድ የሚቀርበውን ዝርዝር የመዋቅር ጥናትና ቻርት በተመለከተ	☑		ዘመኑን በሚዋጁ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ የሚታይ ከሆነ አግባብነት ይኖረዋል
17. መግለጫ አሰጣጥ እና የስብከት ዘዴ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ፣		☒	በሕግ ባለሙያዎች እና የዘመኑን ፖለቲካ፥ የመገናኛ ቴክኖሎጂ ወዘተ ያገናዘብ ብያኔ ተሰጥቶ ከማጽደቅ ውጭ አጀንዳ ሊሆን አይገባዉም
18. አገራዊ ሰላምን በተመለከተ	☑		አገራዊ ሰላምና የአርቶዶክሳውያን እለቂት፥ ስደት፥ የሲኖዶስ በጎ መከፋፈል፥ የመንግሥት የሲኖዶስ ውግዘትን አለማስከበር ተብሎ መያዝ ሲገባው ድፍን ያለ መሆኑ አግባብነት የለዉም
19. የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ግበረ ሰዶማዊነትን በተመለከተ '		☒	የቀኖና የትምህርት፥ የውግዘት ማስተላለፍ እንጂ የሲኖዶስ ወይይት መሆን የማይገባው እጅግ ምአራባዊነት የተጫነው አጀንዳ ነው
20. የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልናና የውስጥ አንድነትን ማጠናከር በተመለከተ	☑		የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና መሠረት የሆኑት የሐዋርያትና የዓለም አቀፍ ጉባኤአት ውሳኔና ቀኖና መከበር፥ የከህነትና የኤጲስቆጶሳት ሲመት ከቀኖና ውጭ መሆን፥ የጳጳሳት ሕገወጥ የንብረት ማፍራት ሂደት፥ የመነኮሳት ከተማ መከተምና ለጵጵስና መሰለፍ፥ የዘር ፖለቲካ አገልጋይ ካህናትና ጳጳሳት መፈጠር ሁሉን ስለሚያካትት ለዚህ ቀኖናዊና ሕጋዊ መፍትሔ ስለ መስጠት ቢባል አግባብነት ይኖረዋል፤ በተቃራኒው “ሲኖዶስ” ይከበር፥ የዘር ጳጳስ ይከበር ከሆነ -- ልዕልና አይገኝም
21. የቋሚ ሲኖዶስ አባላት ምርጫን በተመለከተ	☑		ከነስኝነት፥ ከፍቅረ ንዋይ፥ ከፖለቲካ አገልጋይነት፥ ከፍርሃትና አድርባይነት ነጻ የሆኑ መንፈሳዊ አርበኞቸፍና አሁን ቤተክርስቲያን የገጠማትን ሁለገብ ሥርዓታዊ ጥቃት ያገናዘበ መሥፈርት የሚያሟሉ አባቶችን መምረጥ ከሆነ አግባብነት አለው። በተቃራኒው እንደተለመደው የኮታና የተረኝነት ከሆነ ትርጉም የለዉም።

በዚህ የጥፋት ዘመን አግባብነት ያላቸው የታፈኑ አጀንዳዎች የሚከተሉት ናቸው

1. መንግሥት በቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ በገዳማትና በክርስቲያኖች ላይ ያወጀውን ጦርነት የሚመለከተ
2. የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጥራትና ኦርቶዶክሳዊነትን በሚመለከት
3. በክርስቲያኖች መካከል ግጭትን በሕግ ደረጃ ቀምሮ የሚመራውን የብልጽግና መንግሥትና የሕወሐት ፖለቲካን በሚመለከት
4. የጠጣሱ የቤተክርስቲያን ቀኖናዎችና ሕገወጥ የጎሣ ሲመትን በሚመለከት
5. እልቂት ስለተፈጸመባቸው፥ ስለተፈናቀሉ፥ ስለተሰደዱ፥ በአስገዳጅ ሁኔታ ከእምነት ስለወጡ መእመናንን በሚመለከት
6. ከተሐድሶ መናፍቃን፥ ከጎሣ ፓርቲዎችና መንግሥት ወግነው ስለሚሰሩ ጳጳሳትና መነኮሳትን በሚመለከት
7. ኦርቶዶክስ ለብልጽግናና ለእድግተ አትሆንም የሚለውን ፖሊሲ የሚያራምድ ፖለቲካን ምእመናን የሚመክቱበትን መንግድ ስለማስተባበር
8. የጎሣ ሲኖዶሳት መፈልፈልና የመንግሥት የሲኖዶስን ውግዝት ያለማስፈጸሙን ጉዳይና በመእመናን ትብብር ስለሚፈጸምበት ጉዳእ
9. ከቀኖና ውጭ ከተማ ስለከተሙ መነኮሳት፥ ንብረት ስለሚላፈሩና ዘመድ ስለሚሰበስቡ ጳጳሳትን በሚመለከት
10. የምእመናን ውርጃን፥ ፍቺን፥ ዘረኝነትን፥ ሙስናን ወዘተ በመብት ደረጃ መያዝን ወደ ቀኖና የመመለስ ጉዳይ